# የዶ/ር ሃይሉ አርአያ የታሪክ ፍርደ-ገምድልነት

## ከመዝገቡ ባየህ

ዶ/ር ሃይሉ አርአያ የቀድሞው የኢሰፓ አባል እና የአሁኑ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ም/ሊቀመንበር፣ የጥናትና ምርምር ሃላፊ ለአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ የአማርኛው ክፍል፣ ሚያዝያ 2 ቀን 2002 ዓ. ም የሰጡትን ቃለ-መጠይቅ በትዝብት አዳምጨዋለሁ። ከትዝብትም አልፎ በንዴት።

አንድ ሰው ጥፋት ሲፈጽም በሃይማኖቱም ንስሐ ሲገባ፣ በዓለማዊውም አጥፍቻለሁ ሲል ይቅርታ ማድረግ የተለመደ ነውና፣ የእርሳቸውን ጨፍጫፊው ደርግ እራሱን ወደሲቪልነት የቀየረበት ኢሰፓ አባል መሆን የጎደፈ ታሪክ ችል ብዬ ነበር ያዳመጥኳቸው። ምንአልባት ወደህሊናቸው ተመልሰው ይሆናል በማለት። ክህደታቸው፣ በታሪክ መዋሻታቸው ይህን ትዝብት እንድጽፍ አደረገኝ። በቅድሚያ ግን ደርግ ቀይ ሽብር አውጆ ጭፍጨፋውን ሲያካሂድ በከተማ ከአገዛዙ ጋር በመመሳሰል፣ በሜዳም ጦር በመምዘዝ የኢሕአፓን አባላት የገደለውና አሁንም የዚህኑ ድርጅት አባላት እያሳደደ የአፈናና ግድያው ሰለባ የሚያደርገው ወያኔ በሰማዕታቱ ስም ለመነገድ የሞራልም የሕግም ብቃት እንደሌለው ማስመር እሻለሁ። በማስከተልም እስከወዲያኛው በታሪክ ላይ ለማበል ቃል-ኪዳን ለገቡት ለዶ/ር እና መሰሎቻቸው እንዲህ እላቸዋለሁ - ህሊና የሚባለውን ፈጥሮባቸው ከሆነ።

- ዶክተሩ የነጭ ሽብር ሰለባዎች የሚሏቸው የገዢው መንግስት ነፍሰ-ገዳዮች ባልሞት ባይ ተጋዳይነት እርምጃ ሳይወሰድባቸው በፊት ከግድያና አፈና ድርጊታቸው እንዲታቀቡ በኢሕአፓ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸው ነበር። እርምጃም የሚወሰድባቸው ከድርጊታቸው አልታቀብ ሲሉ ነበር። አዎ! ደርግ እና ተባባሪዎቹ ግን ቀይ ሽብር ብለው ጭፍጨፋ የሚያካሂዱት ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን ለመጠየቅ ሰላማዊ ሰልፍ በሚያደርጉ፣ ከተቃዋሚው ጎራ ተሰልፈው በሰላማዊ መንገድ በሚታገሉት የሕዝብ ልጆች ላይ ነበር። የተቃዋሚው አባል ወይም ሀሳብ ደጋፊ ናቸው የሚሏቸውን ከየቤታቸው፣ ከየመንገዱና ከሌሎችም ቦታዎች እያደኑ፣ ካሰሯቸው በሁዋላ ነበር የጭፍጨፋ ጥማታቸው ጭዳ የሚያደርጓቸው። ዛሬ ወያኔ እነ ሽበሬ ደሳለኝንና ብዙ ሽህዎችን፣ እነተስፋዬ ታደሰ፣ አሰፋ ማሩ፣ ወዘተን እንደገደለው፣ እነአበራሽ በርታን፣ እነብርቱካ ሚደቅሳን፣ እነጸጋዬ ደብተራውንና ሌሎችንም ብዙ ሺህዎች አፍኖ በጨለማ እስር ቤቶቹ እንደሚያሰቃየው ወይም መዳረሻቸውን እንዳጠፋው፣

- እሳቸው የነጭ ሽብር ሰለባዎች የሚሏቸው የገዢው መንግስት ነፍሰ-ገዳዮችማ ባልሞት ባይ ተጋዳይነት እርምጃ ሲወሰድባቸው ደርግ በክብር ቀብሯቸዋል። ያደፋውና ጸረ-ሕዝብ ድርጊታቸው - ከደርግ ጋር መወገናቸው - እንደገድል ተቆጥሮ በሕዝብ መገናኛዎች ተወድሶላቸዋል። ከመቃብርም ቦታ እየተመረጠ - ለምሳሌ የአዲስ አበባው ቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ያስታውሷል - ወግ ላለው ቀብር በቅተዋል። ጥቁር አንበሳ ፊት ለፊት ያለውን ዓይነት ሀውልቶችም ወታደራዊ አገዛዝ እና ተባባሪዎቹ ያደረጉትን ጭፍጨፋና ያገኙትን የበላይነት ለማሰብ ያቋቋሟቸው ናቸው። ስልጣን ለሕዝብ በማለት ወታደራዊውን አገዛዝ የታገሉት ሰማዕታት ግን አስከሬናቸው በየመንገዱ ተሰጥቶ እየዋለ ለህዝብ ማስፈራሪያ ሆኗል። በየፈፋ ሜዳው እየተጣለ የአውሬ እራት ሆኗል። እናት፣ አባት፣ ወንድም፣ እህት፣ ሚስት፣ ባል በአካሉ ክፋይ አስከሬን ላይ "ያድሃሪ ደም ሲፈስ፣ አቤት ደስ ሲል" እያሉ እንዲዘፍኑ ተገደዋል። ለተገደሉበት ጥይት ገንዘብ እየከፈሉ አስከሬናቸው የተሰጣቸው ቤተሰቦቻቸው እንደወጉ ከዘመድ አዝማድ ጋር ሳይሆን ለብቻቸው ቀብረው፣ እየየም ማለት እንዳይችሉ ተከልክለው፣ ቤታቸውን በመዝጋት ሀዘናቸውን ለብቻቸው ተወጥተዋል።

- እሳቸው የነጭ ሽብር ሰለባዎች የሚሏቸው የገዢው መንግስት ነፍሰ-ገዳዮችማ ባልሞት ባይ ተጋዳይነት እርምጃ ሲወሰድባቸው ዘመዶቻቸው ብቻ ሳይሆኑ እነሱ የገደሏቸው የቀይ ሽብር ሰማዕታት ቤተሰቦችን ጨምሮ ሕዝቡ በግድ እየተገደደ ወጥቶ ለቅሷቸውን እንዲያደምቅ ተደርጓል፣

- እሳቸው የነጭ ሽብር ሰለባዎች የሚሏቸው የገዢው መንግስት ነፍሰ-ገዳዮችማ ባልሞት ባይ ተጋዳይነት እርምጃ ሲወድባቸው፣ ልጆች፣ ሚስት፣ ባል ወዘተዎቻቸው በህዝብ ሀብት ሲጠወሩ፣ የትምህርትም ሆነ የስራ ዕድል በቅድሚያ እየተሰጣቸው አንደኛ ደረጃ ዜጋ ሆነው ተጠቅመዋል። እነሱ የገደሏቸው የቀይ ሽብር ሰማዕታት ቤተሰቦች ግን "የጸረ-አብዮት" ወላጆች፣ እህት፣ ወንድም ወዘተ እየተባሉ የአፈናውና የግድያው ሰለባ ሆነዋል፣ ሲያንስም ያለጧሪ ረዳት ቀርተው እንደ ሁለተኛ ዜጋ እየታዩ ለከፋ ኑሮ፣ አእምሯዊ ሰቆቃና ሃዘን ተዳርገዋል፣

- የሚሉትን ውሃ የማይቋጥር እና ለሁለቱም ማለትም የገዢው ወገን ለጨፈጨፋቸውም ሆነ ጭፍጨፋውን በመቃወም እና የአጠፌታ መከላከል ሲወሰድ እርምጃ ለተወሰደባቸው ሰዎች አንድነት ሃውልት መቆም አለበት ሲሉስ ለጂዎች እና ለሂትለር ናዚ ወታደሮችም ሃውልት መቆም አለበት እንደማለት አይሆንም? ለጣሊያን ባንዳ ሆነው በውጊያው ለሞቱት እና

በአርበኝነት ጠላትን ሲፋለሙ ለወደቁት፣ በስመ ኢትዮጵያዊነት አንድ ላይ ሃውልት ይቁምላቸው እንደማለት አይሆንም? ወይም በአሁኑ የሀገራችን ሁኔታ ወያኔንን ሲፋለሙ የሚወድቁ ሰማዕታት እና አገዛዙን ለማቆየት ሲሰሩ በተቃዋሚ ኢትዮጵያዊ ሃይል እርምጃ የተወሰደባቸው፣ ወደፊትም የሚወሰድባቸው አፋኞች እኩል የታሪክ ክብር ሊሰጣቸው ይገባል ማለት አይሆንምን?

- በአጭር ምሳሌ ትዝብቴን ልደምድምና የ1997ኡን ምርጫ ተከትሎ በወያኔ ከታሰሩት ሰላማዊ ሰልፈኞች ጎን በመቆሟ በአገዛዙ የተቀጠፈችው ሽብሬ ደሳለኝ አቅሙ ኖሯት ሊገድላት የመጣውን የአገዛዙን አፋኝ ብትገድለው፣ እሷም እሱም ተገዳደሉ ተብሎ እንዲህ እንደዋዛ መዘከር አለባቸውን? ጨቋኝ አገዛዝን በመቃወም መታገልና በትግሉም መሰዋትስ በታሪክ ሚዛን ከገዳዩ እኩል ክብር ከተሰጣቸው ለተተኪው ትውልድ ምን የገድል ውርስ ነው የምናስተላልፈው? የትላንቶቹን እምቢ ለመብቴ ታጋይ ሰማዕታት ከገዳዮቻቸው እኩል የታሪክ ሚዛን ሰጥተን እያንኳሰስን፣ ዛሬ የትግሉን ችቦ ተረክበው ትግሉን የሚቀጥሉ ታጋዮች ማፍራት ይቻላልን? ትላንት ደርግ በስልጣኔ አትምጡ፣ ተቃዋሚዎች ደግሞ ስልጣን ለሕዝብ አስረክብ ብለው ነበር ትግሉ። ወይም የደርግ ጭፍጨፋ ደጋፊ አንሆንም ስላሉ ካለሆነም ላይሆኑ ይችላሉ በሚል በመጠርጠራቸው። አለዚያም ከዘውዳዊው አገዛዝ ጋር የደም ወይም የስልጣን ንክኪ አላቸው በሚል በመወንጀላቸው። አልፎም ሀብት ወይም ሚስቶቻቸውን ለመቀማት ስለተፈለገ። ዛሬም ወያኔ የደርግን የስልጣን ወንበር ወርሶ ጸረ-ሕዝብና ጸረ-ኢትዮጵያ አገዛዝን በመቀጠሉ ሕዝባዊው የሰብአዊ መብትና የዴሞክራሲ ትግል የሚካሄድ መሆኑን ልብ ልንል ይገባል።

እንደዚህ ህሊና ቢስ የሆነ የታሪክ ፍርደ-ገምድል ሆነውስ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ መልካም ራዕይ አላሚ ነኝ ማለት ይችላሉ - የትላንቱ ኢሰፓ የዛሬው የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ም/ሊቀመንበር፣ የጥናትና ምርምር ሃላፊ ዶ/ር ሃይሉ? እየተስተዋለ እንጂ ዶ/ር?! የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሰራተኛ ማህበር መሪ የነበረችው እና ተይዛ የተገደለችው ዳሮ ነጋሽ፣ አርግዛው የነበረውና ሆዷ ተቀዶ ወጥቶ የተገደለው ልጇ፣ ሁዋላ ከተገደለው ገዳያቸው ጋር አብሮ የታሪክ ክብርና ዝክር ይሰጠው ነው የሚሉን?! በካድሬ አስገዳጅነት ሰልፍ የወጣው እና የአስታጥቁን መፈክር የተባረቀበት ሕዝብ በወታራዊው አገዛዝ የተጨፈጨፈው በራሱ ጥያቄ ነው የሚሉን? ግደሉኝ በሎ ስለጠየቀ ነው አገለግለው የነበረው አገዛዝ የገደለው የሚሉን? አዲዮስ ሰብአዊነት!